

# መንፈሳዊ ጡንቻ

14-2

## ጎበዞች

"ጎበዞች ሆይ ክፉን አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ" ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ጎበዞችን ሲገልጻቸው 1ኛ፥ ጠንካሮች፥ 2ኛ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ያወቁ፥ 3ኛ፥ ክፉውን ያሸነፉ ይላቸዋል። አንድ ሰው ጎበዝ ከመሆን ደርጃ ሲደርስ አምስት ነገር በአጠቃላይ ያውቃል። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በሕጻንነት ደረጃ በነበረበት ጊዜ የሚያውቃቸው፥ ይኸውም ኃጢአቱ ይቅር እንደተባለለትና ሰማያዊ አባቱን እንደሚያውቅ ነው። አሁን ደግሞ ጎበዝ በሆነበት ደረጃ የሚያውቃቸው 3 ነገሮች አሉ፤ ይኸውም ብርቱነቱን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቁንና ክፉውን መሸነፉን ነው። በአጠቃላይ አምስት ነገሮችን ያውቃል ማለት ነው። ኢያሱም በልቡ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰወረ። ያም ደግሞ የድሉ ምክንያት ሆነለት። በ1ኛ ዮሐንስ 2፥14 ላይ ጎበዞች አሸናፊ የሆኑበትን ምክንያት ሲገልጽ እንደዚህ ይላል። "ብርቱዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስላሸነፋችሁ እጽፍላችኋለሁ"። ኢያሱ የእግዚአብሔርን ቃል በልቡ በመሸሸጉ ምክንያት አሸናፊ እንደሆነ፥ እኛም ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በማደግ በሚያጋጥመን ፈተናና ትግል ሁሉ ድል ማደርግ እንችላለን። ኢያሱ መንፈሳዊ ጡንቻውን ሊያዳብር የቻለው በእግዚአ ብሔር ቃል ስለሆነ በመሪነቱ ድል አደረገ። እንደዚሁ ደግሞ እኛም ወሰን በሌለው በክርስቶስ ላይ መሠረታችንን ካደርግን፥ እንደ ቃሉም ከታዘዝነው የሚያጋጥመንን መከራና ችግር ማሸነፍ እንችላለን።

## አባቶች

ትክክለኛውን ቅደም ተከተል ከተከተልን፥ በመጀመሪያ ልጆች ወይንም ሕጻናት ቀጥሎ ጎበዞች፥ በመጨረሻ ደግሞ ሽማግሌዎች ወይም አብቶች እንሆናለን። ወጣቶች ልጆች የሚኖራቸውን እውቀት ይኸውም፥ ለኃጢአታቸው ይቅርታ እንደተሰጣቸውና እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችቸው እንደሆነ ያውቃሉ። እንዲሁም ደግሞ አባቶች ወጣቶች የሚኖራቸውን እውቀትና ኃይል ይኖራቸዋል። ያም "ብርቱ ዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉንም ስላሸነፋችሁ እጽፍላችኋለሁ" በሚል ቃል መሠረት ነው።

ልጆችና ጎበዞች በነበሩበት ጊዜ ተምረው ያለፉት ፍሬ ሃሳብ ቢኖርም፥ ሽማግሌዎች በሚሆኑበት ጊዜ ደግሞ ሌላ ከዚያ ጠለቅ ያለ እውቀት ይኖራቸዋል። ለዚህ ነው "ከመጀመሪያ የነበረው አውቃችኋልና" የሚለው"። "ከመጀመሪያ" የሚለው ሃሳብ ወደ እግዚአብሔር አብ ያመለክታል። እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ ብቻ ሳይሆን፥ ለምን እንዳደርገ ጥልቀት ያለው እውቀት ይኖራቸዋል። ሥራቸው ጠለቅ ብሎ በመሄድ ዘላለማዊውን የእግዚአብሔርን እውነት ያውቃሉ።

በ1ኛ ዮሐንስ 2፥12 ላይ አባቶች ብሎ ሲናገር ልጆች የመውለድና የማሳደግ እንዲሁም የቤተሰብ መመስረት ችሎታ እንዳላቸው ይገልጻል። ይህም መንፈሳዊ ትምህርት አለው። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አባቶች ከመሆን ደርጃ የደርሱ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ይመራሉ። ስለሆነም መነፈሳዊ ልጆች፣ የልጅ ልጆችና ከዚያም በላይ ይኖራቸዋል። ቤተሰብ የመመሥረትና የማሳደግን ስነሥርዓትን የማስያዝና

የማስጠበቅ እንዲሁም ኃላፊነት እንዲይዙ የማደረግ ችሎታ አላቸው። እግዲህ ማንኛውም ክርስቲያን በሕይወቱ መነፈሳዊ ብስለትና እድገት እንዲታይበት ያስፈልጋል። ዓለም በእኛ ሕይወት ለማየት የሚፈልገው እምነት በሥራ ሲተረጎም ነው። ኢየሱስ ደግሞ በእኛ ሕይወት ማየት የሚፈልገው መስቀሉን ተሸክመን በደስታ መራመድ መቻላችንን ነው። እንግዲህ መነፈሳዊ ጡንቻችንን ለማሳደግና ብርቱዎች ለመሆን እራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል ማሳደግ እንዳለብን በዚህ በአጭር ትምህርታችን መገንዘብ ችለናል።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**